የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 6/0/91/16
ቀን/Date መስከረም 1 2 2016

**የጉምሩክ ስነ-ስርአት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ፅ/ቤቶች በሙሉ**

**<u>በያሉበት</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>ተቀባይነት ያለው የስሪት ሀገር መግለጫ ያልቀረበባቸው ገቢ ዕቃዎች ስለሚስተናገዱበት ሁኔታ</u>**

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 107 ንኡስ አንቀፅ 2 በመደበኛ የንግድ ግብይት (ማለትም ከቀረጥ ነጻ ስምምነቶች ውጭ በሆነ መደበኛ ንግድ) ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በማሸጊያቸው ላይ የስሪት ሀገራቸው በቀላሉ ሊፋቅ፣ ሊነሳና ሊለወጥ በማይችል ሁኔታ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሊገለፅባቸው እንደሚገባና በዚህ አግባብ ተቀባይት ያለው የስሪት ሀገር መግለጫ ያልቀረበባቸው ዕቃዎች ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የሚደነግግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህንንም ህግ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ከቅ/ፅ/ቤቶች የሚለያይ ስለመሆኑ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ሆኖም የሀገሪቱ የውጪ ምንዛሬና ሌሎች ወጪዎች ወጥቶባቸው ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች የስሪት ሀገር መግለጫ አልቀረበባቸውም በሚል ብቻ ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ ማድረግ የሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ከፍተኛ በመሆኑ ህጉ ተፈፃሚ ሳይደረግ ቆይቷል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የስሪት ሀገር አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 134/2010 አንቀፅ 15 ንዑስ ቁጥር 2 ተፈፃሚነት እንዲዘገይ በቁጥር 1/204/11 ቀን 02/01/2011 በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በተጻፈ ሰርኩላር የተወሰነ ሲሆን በዚሁ መሰረት *ተቀባይት ያለው የስሪት ሀገር መግለጫ ያልቀረበባቸው ገቢ ዕቃዎች የስሪት ሀገር ከላኪ ሀገር በተሰጠ የስሪት ሀገር ሰርተፍኬት መሰረት* እንደሚወሰን ይገልጻል፡፡ ሆኖም የመደበኛ ንግድ የስሪት ሀገር ሰርተፍኬት ተመሳስሎ ለመስራት እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጥ ከመሆኑ አኳያ ተአማኒነቱ አነስተኛ በመሆኑ የስሪት ሀገር ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱን ብቻ ታሳቢ በማድረግ የስሪት ሀገር ውሳኔ መስጠት ተገቢ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በቁጥር 1/204/11 በቀን 02/01/2011 ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተላለፈው ሰርኩላር የተሻረ መሆኑን



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordcpr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

እየገለፅን ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የስሪት ሀገር ሰርተፍኬት በተመለከተ ቀጥሎ በተቀመጠው መሰረት ተፈፃሚ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

1) በመደበኛ የንግድ ግብይት መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው ተቀባይነት ያለው የስሪት ሀገር መግለጫ ያልቀረበባቸው ገቢ ዕቃዎች የስሪት ሀገር ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ካላቸው ሀገራት እንደመጣ ተቆጥሮ የዕቃው ዋጋ በዚህ አግባብ እየተወሰነ መስተንግዶ እንዲሰጥ ፤
2) በቀረጥ ነጻ ወይም ቀረጥ ቅናሽ የንግድ ስምምነቶች (ለምሳሌ፡ የኮሜሳ እና ኢትዮ-ሱዳን ስምምነቶች) እንዲሁም በቀጣይ ተግባራዊ ለሚሆነው የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ስምምነት መሰረት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎች የስሪት ሀገር የሚወሰነው በስምምነቶቹ ድንጋጌዎች መሰረት ብቻ በመሆኑ ከስሪት ሀገር መግለጫ ጋር በተያያዘ ከላይ የተጠቀሰው የመደበኛ ንግድ እቃዎች ድንጋጌ የማይመለከታቸው መሆኑ ታውቆ በስምምነቶቹ የተቀመጡ የስሪት ሀገር ደንቦችን ታሳቢ በማድረግ እና ከዲ/ዮን ጋር የቀረበው የስሪት ሀገር ሰርተፍኬት *<u>ከላኪ ሀገር ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ ትክክለኛ የስሪት ሀገር ማረጋገጫ ሰርተፍኬት</u>* ስለመሆኑ ማጣራት በማድረግ መስተናገድ አለባቸው፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 2
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.2

**<u>እንዲያውቁት</u>**

- ለክቡር ኮሚሽነር

**<u>ግልባጭ</u>፡-**

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤ/ት
- ለታሪፍ ምደባና ለስሪት ሀገር አወሳሰን ዳ/ት
  **<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>**